## ትምህርት ሁለት (የመጽሐፍ ቅዱስ መግቢያ)

### የቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር እንዴት ይገለጻል? ቅዱሳት መጻሕፍት የትኞቹ ናቸው?

በትምህርት አንድ ላይ ለማብራራት እንደተሞከረው የቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር በግሪክና በእንግሊዝኛ "ካኖን" ተብሎ ይጠራል። "በካኖን" ውስጥ የተዘረዘሩት የብሉይና የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በሙሉ (ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ዮሐንስ ራእይ) እግዚአብሔር ያስጻፋቸው ወይም ሰዎች በእግዚአብሔር መንፈስ ተሞልተውና ተመርተው የጻፏቸው ናቸው፤ ዋና የክርስቲያን መመሪያ ናቸው (ሮሜ. 15፡4፤ 2ጢሞ. 3፡16-17)። በዚህም ምክንያት ቅዱሳት መጻሕፍት በመባል ይታወቃሉ። እነዚህ መጻሕፍት ዝርዝራቸውና ተቀባይነታቸው በሁሉም ሃይማኖቶች ዘንድ አንድ አይደለም (አንድ ዓይነት ወይም ወጥ የሆነ ተቀባይነት የላቸውም)።

### ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝራቸውና ተቀባይነታቸው በሁሉም ሃይማኖቶች ዘንድ አንድ ዓይነት ካልሆነ ይህ የቁጥርና የአቀባበል ልዩነት እንዴት ሊገለጽ ይችላል?

ይህንን ጥያቄ ለመመለስ የካቶሊክ፣ የኦርቶዶክስና የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ዘንድ ያለው የቅዱሳት መጻሕፍት አቀባበልና የቁጥሮቹ መብዛትና ማነስ ማየቱ ግድ ነው።ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተካተቱትን 27 መጻሕፍት ይቀበላሉ። ልዩነታቸው ብሉይ ኪዳን ውስጥ በተካተቱትና አንዳንዶች(ለምሳሌ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤ/ክ) አዲስ ኪዳን መጻሕፍት ላይ በተጨማሪ በሚያካትቱአቸው መጻሕፍት ላይ ነው። የሚቀበሉአቸውም የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው።ወንጌላት፦ (ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ፣ ዮሐንስ)፤ የሐዋርያት ሥራ፤ የጳውሎስ መልእክቶች፤ የጴጥሮስ፣ የዮሐንስ፣ የያዕቆብና የይሁዳ መልእክቶች እና የዮሐንስ ራእይ ናቸው።

#### ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን፦

ከ27ቱ የአዲስ ኪዳንና ከ39ኙ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍቶች በአጠቃላይ ከ66ቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ጋር የምትቀበላቸው ሰባት ሌሎች መጻሕፍት አሉ። እነርሱም ድኅረ ቀኖና(ዲዮትሮ ካኖኒካል) ተብለው ሲጠሩ 66ቱ ደግሞ "ፕሮቶ ካኖኒካል" ይባላሉ። በጠቅላላው 73 መጻሕፍት ሲሆኑ ሁሉም እኩል ተቀባይነት አላቸው። ሰባቱ መጻሕፍት በ1989 ዓ. ም. በአማርኛ ታትመው ወጥተዋል። እነዚህ ሰባት መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው፦መጽሐፈ ጦቢት፤ መጽሐፈ ዮዲት፤ መቃብያን 1፤ መቃብያን 2፤ መጽሐፈ ጥበብ፤ መጽሐፈ ሲራክ እና መጽሐፈ ባሮክ ናቸው።

**አስተውል፦** *ሁለቱ የመቃብያን መጻሕፍት በኦርቶዶክስ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጠቀሱት ሦስቱ የመቃብያን መጻሕፍት ጋር በስም እንጂ በይዘት አመሳሰሉም።*

**የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን፡-** 81 መጻሕፍትን ትቀበላለች፡፡ በመጽሐፈፍትሐ ነገሥት በግእዝ የተዘረዘሩት መጻሕፍት አቆጣጠራቸው እንደሚከተለው ነው፡፡

**ሀ/ ብሉይ ኪዳን**

1) ኦሪት (ኦሪት ማለት አምስቱ የኦሪት ወይም የሙሴ መጻሕፍት) እና፣ ኢያሱ፣ መሳፍንት፣ ሩት
2) ዮዲት፤ 1ኛና 2ኛ ሳሙኤል፤ 1ኛና 2ኛ ነገሥት እና ዜና መዋዕል፤ ዕዝራ፡ካልዕ፤ ዕዝራ ሱቱኤል፤ አስቴር፤ ጦቢት፤ መቃብያን (ሦስት መጻሕፍት)፤ ኢዮብ፣ መዝሙረ ዳዊት፤ የሰለሞን መጻሕፍት(እነዚህም መጽሐፈ ምሳሌ፤ተግሳጽ፤ጥበብ፤መክብብ፤ መኃልይ ናቸው)፡፡
3) ነብያት(4 ዐበይት ወይም ታላላቅ ነብያት እና 12 ደቂቀ ወይም ታናናሽ ነብያት)፤
4) ሲራክ፤ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን፤ ኩፋሌና ሄኖክ፤

**የብሉይ ኪዳን ድምር** 46 ነው፡፡

**ለ/** **አዲስ ኪዳን**

1. ከማቴዎስ ጀምሮ እስከ ዮሐንስ ራእይ፡- በአጠቃላይ 27 መጻሕፍት ናቸው፡፡
2. ሲኖዶስ(ሲኖዶስ በመባል የሚታወቁት ሥርዐተ ጽዮን፤ትእዛዝ፤ግጽው፤ አብጥሊስ)፡- 4 መጻሕፍት፤
3. መጽሐፈ ኪዳን፡- በአጠቃላይ 2 መጻሕፍት፤
4. ቀሌምንጦስና ዲድስቅልያ፡- በአጠቃላይ 2 መጻሕፍት፡፡ በዚህ መሠረት ጠቅላላ **አዲስ ኪዳን 35** ሲሆኑ ጠቅላላ **የብሉይ ኪዳን46** ናቸው፤ ጠቅላላ ድምራቸው **81** ነው፡፡

**የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት**፡- የመጀመሪያዎቹ 39ኙ የብሉይና 27ቱ የአዲስ ኪዳን መጻሐፍት በአጠቃላይ 66ት መጻሕፍት ይቀበላሉ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩት ልዩነቶች እንዳሉ ሆነው ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት (ካቶሊክ፣ ኦርቶዶክስና ፕሮቴስታንት) በጋራ ወይም በተመሳሳይ መልኩ የተቀበሏቸው የቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር እንደሚከተለው ይቀርባል፡-

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ኦሪት ዘፍጥረት | 14 | ሁለተኛው መጽሐፈ ዜና መዋዕል | 27 | ትንቢተ ዳንኤል |
| 2 | ኦሪት ዘጸአት | 15 | መጽሐፈ ዕዝራ | 28 | ትንቢተ ሆሴዕ |
| 3 | ኦሪት ዘሌዋውያን | 16 | መጽሐፈ ነህምያ | 29 | ትንቢተ አሞጽ |
| 4 | ኦሪት ዘኁልቅ | 17 | መጽሐፈ አስቴር | 30 | ትንቢተ ሚክያስ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 5 | ኦሪት ዘዳግም | 18 | መጽሐፈ ኢዮብ | 31 | ትንቢተ ኢዩኤል |
| 6 | መጽሐፈ ኢያሱ | 19 | መዝሙረ ዳዊት | 32 | ትንቢተ አብድዩ |
| 7 | መጽሐፈ መሳፍንት | 20 | መጽሐፈ ምሳሌ | 33 | ትንቢተ ዮናስ |
| 8 | መጽሐፈ ሩት | 21 | መጽሐፈ መክብብ | 34 | ትንቢተ ናሆም |
| 9 | አንደኛው መጽሐፈ ሳሙኤል | 22 | መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን | 35 | ትንቢተ ዕንባቆም |
| 10 | ሁለተኛው መጽሐፈ ሳሙኤል | 23 | ትንቢተ ኢሳይያስ | 36 | ትንቢተ ሶፎንያስ |
| 11 | አንደኛው መጽሐፈ ነገሥት | 24 | ትንቢተ ኤርምያ | 37 | ትንቢተ ሐጌ |
| 12 | ሁለተኛው መጽሐፈ ነገሥት | 25 | ሰቆቃው ኤርምያስ | 38 | ትንቢተ ዘካርያስ |
| 13 | አንደኛው መጽሐፈ ዜና መዋዕል | 26 | ትንቢተ ሕዝቅኤል | 39 | ትንቢተ ሚልክያስ |

**እነዚህ ከላይ የተገለጹት የብሉይ ኪዳን መጻሐፍት በአራት ክፍሎች ይመደባሉ፡-**

**ብሉይ ኪዳን**

| **1) የሕግ መጻሕፍት (የኦሪት ወይም የሙሴ መጻሕፍት)** | **2) የታሪክ መጻሕፍት** | **3) የመዝሙርና የጥበብ መጻሕፍት** | **4) የትንቢት መጻሕፍት** |
|---|---|---|---|
| ዘፍጥረት | መጽሐፈ ኢያሱ | መጽሐፈ ኢዮብ | ትንቢተ ኢሳይያስ |
| ዘጸአት | መጽሐፈ መሳፍንት | መዝሙረ ዳዊት | ትንቢተ ኤርምያስ |
| ዘሌዋውያን | መጽሐፈ ሩት | መጽሐፈ ምሳሌ | ሰቆቃው ኤርምያስ |
| ዘኁልቅ | 1ኛ መጽሐፈሳሙኤል | መጽሐፈ መክብብ | ትንቢተ ሕዝቅኤል |
| ዘዳግም | 2ኛ መጽሐፈሳሙኤል | መኃልየ መኃልይ | ትንቢተ ዳንኤል |
| | 1ኛ መጽሐፈ ነገሥት | | ትንቢተ ሆሴዕ |
| | 2ኛ መጽሐፈ ነገሥት | | ትንቢተ ኢዩኤል |
| | 1ኛ ዜና መዋዕል | | ትንቢተ አሞጽ |
| | 2ኛ ዜና መዋዕል | | ትንቢተ አብድዩ |
| | መጽሐፈ ዕዝራ | | ትንቢተ ዮናስ |
| | መጽሐፈ ነህምያ | | ትንቢተ ሚክያስ |
| | መጽሐፈ አስቴር | | ትንቢተ ናሆም |
| | | | ትንቢተ ዕንባቆም |
| | | | ትንቢተ ሶፎንያስ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | ትንቢተ ሐጌ |
| | | | ትንቢተ ዘካርያስ |
| | | | ትንቢተ ሚልክያስ |

**መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ መጻሕፍትን ያካተተ (የያዘ) ትልቅ ቅዱስ መዝገብ ከሆነ በምን ዓይነት መልኩ ሊከፋፈል ይችላል?**

መጽሐፍ ቅዱስ ከኦሪት ዘፍጥረት ጀምሮ በዮሐንስ ራእይ እንደሚጨርስ ይታወቃል። ይህ ቅዱስ መጽሐፍ ብሉይ እና አዲስ ኪዳን በመባል የሚጠሩ ሁለት ትልልቅ ክፍሎች አሉት፤ እነዚህ ሁለቱ ኪዳኖች ከላይ እንደተገለጸው በውስጣቸው የራሳቸው የሆነ አከፋፈል አላቸው።

**ኪዳን ማለት ምን ማለት ነው?**

ኪዳን ማለት በተለያዩ ወገኖች መካከል የሚደረግ ውል፣ ቁም ነገር፣ የፍቅርና የአንድነት መሐላ፣ ሰላማዊ ሕግ፣ ሁለቱን ወገን አንድ የሚያደርግ፣ ስለ ረብና ጥቅም በተስፋ የቆመ የተጻፈ ሥርዓት፣ ቢያፈርሱት ጉዳትና ጠብ የሚያመጣና ጥቅም የሚያሳጣ የሚለውን ትርጉም እንደሚሰጥ ከሊቃውንቶች መዝገበ ቃላት እንረዳለን። በአጠቃላይ ኪዳን በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ወገናት መካከል የሚፈጸም ውል ነው።

**ብሉይ ኪዳን ምን ማለት ነው?**

**ብሉይ ኪዳን፦** ብሉይ ማለት ያረጀ፣ ጥንታዊ፣ ቀዳማዊ፣ የድሮ፣ የቀድሞ፣ የፊት ማለት ነው። ከላይ ከተገለጸው በተጨማሪ ብሉይ ኪዳን የሚያመለክተው እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ በሙሴ አማካይነት የሰጣቸው ቃል ኪዳን ነው (ዘጸ 20:1-17፤ 34:28፤ ዘዳ 4:13)። ሕዝቡ እግዚአብሔር የተናገራቸውን ቃሎች ሁሉ እናደርጋለን ሲሉ ሙሴ መሥዋዕትን ሠውቶ ደሙን በሕዝቡ ላይ በመርጨት ቃል ኪዳኑን አጸና (ዘጸ 24:1-8)። ቃል ኪዳኑም እንዲፈጸም ትእዛዝ፣ ሥርዓትና ፍርድ ተሰጡ (ዘዳ 5:31)። ይህም ቃል ኪዳን ከመጀመሪያው ጀምሮ ጊዜያዊ መሆኑን ታወቀ (ዘዳ 18:15፤ ኤር 31:31)፤ አዲስ ኪዳንም ስለገባ ብሉይ ኪዳን አሮጌ ተባለ። በአጠቃላይ ብሉይ ኪዳን ከመጀመሪያው ፍጥረት መፈጠር ጀምሮ እስከ ክርስቶስ መወለድ ድረስ የነበረው የሰዎችንና የእግዚአብሔርን ግንኙነት የሚናገር ነው። የብሉይ ኪዳን አከፋፈል በተመለከተ ከላይ "ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝራቸውና ተቀባይነታቸው በሁሉም ሃይማኖቶች ዘንድ" የሚገልጸውን ይመልከቱ።

**ብሉይ ኪዳን ምን ያህል ዓመታትን ወይም ዘመናት የሚሸፍን ታሪክ እንደሚገልጽ ይታወቃልን?**
**በታሪክ ሂደት ውስጥ ብሉይ ኪዳን የሚተርካቸው ነገሮች በዓመታት ከፋፍሎ ማየት ይቻላልን?**

በእርግጥ ከዘጠኝ መቶ ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት የሆኑት የድርጊቶች ዓመት ወይም ወቅት በትክክል ለመወሰን አንችልም። በእስራኤል የዓመት አቆጣጠር እስራኤላውያን ከግብጽ የወጡበት የኒሳን ወር የመጀመሪያ ሆኖ ይቆጠራል(ዘጸ 12፡12)። ሆኖም ሕዝቡ በግብርና ስለሚኖሩ አጨዳ ሲጨርሱ የዓመት መለወጫ በዓልን ያከብሩ ነበር(ዘጸ 23፡16፣ 34፡22)። ብዙ ጊዜ በወሩ ሳይሆን በግብርና ሥራ ጊዜው ይገለጣል(ዘኑ. 13፡20፣ ሩት 1፡22)። በጥንት ዘመን እንደ ከተማ መቆርቆር፣ እንደ ምድር መናወጥ፣ ከመሳሰሉ ከታወቁ ሁኔታዎች በመነሣት ዓመታት ይቆጠሩ ነበር(አሞ 1፡1)። በዚህ ምክንያት በየጊዜው የተፈጸሙት ድርጊቶች ከክርስቶስ ልደት ወዲህ ካለው አቆጣጠር ጋር ማዛመድ ያዳግታል።

ነገር ግን በተለይ ከዘጠኝ መቶ ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት የሆኑትን ድርጊቶች የተከናወኑበትን ትክክለኛ ዓመት ወይም ወቅት በትክክል ለመወሰን ባንችልም ተቀራራቢ ሊሆን ይችላል ተብለው በሊቃውንቶች ዘንድ የሚገመቱ ዓመታት መግለጽ ይቻላል። በዚህም መሠረት ለምሳሌ የእስራኤል ሕዝብ ከግብጽ አገር የወጡበት ዓመቱ አንዳንዶች ከክርስቶስ ልደት በፊት 1445 ሌሎች 1280 መሆኑን ይገምታሉ። አብርሃም ከ2ሺህ-1850 ገደማ ከክርስቶስ ልደት በፊት እንደኖረ ይታሰባል። ከአብርሃም በፊት የኖሩትን ሰዎች ምን ያህል ጊዜ እንደኖሩ አይታወቅም። አቆጣጠሩ የተለያየ በመሆኑ አንዳንድ ሊቃውንት ከአዳም እስከ ክርስቶስ ድረስ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዓመት ይሆናል ይላሉ። ነገር ግን ይህ የተረጋገጠ አቆጣጠር አይደለም።

ከአዳም ጀምሮ ያለው የብሉይ ኪዳን አከፋፈል፣ ልዩ ልዩ ቢሆንም በሊቃውንት ጥናት መሠረት በስምንት ክፍለ ዘመን ይመደባል። ከአዳም ጀምሮ የነበሩት ዋና ዋና ሰዎች፣ አምልኮና ድርጊቶች በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ነው።

የትምህርቱ አዘጋጅ፡- አባ ምሥራቅ ጥዩ

አስተባባሪ፡- አቶ ተስፋዬ ባደገ

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከመለሱ በኋላ ወደ ሀገረስብከቱ የተልእኮ ትምህርት ዝግጅት ክፍል ይላኩት።**

**የተማሪው/ዋ ስም ----------------------------------ኮድ-------- ቁምስና-------------------ውጤት---------**

1) ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ከ27ቱ የአዲስ ኪዳንና ከ39ኙ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትበተጨማሪ የምትቀበላቸው መጻሕፍት ምን በመባል ይታወቃሉ? እነዚህ መጻሕፍት የቶኞቹ ናቸው?

2) በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተካተቱት 27ቱ ቅዱሳን መጻሕፍት በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ተቀባይነት አላቸው፤ ነገር ግን አንዲት ቤተ ክርስቲያን ለየት ባለ መልኩ ከ27ቱ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በተጨማሪ ሌሎች ተጨማሪ መጻሕፍት ታካትታለች። ይህች ቤተ ክርስቲያን የትኛዋ አብያተ ክርስቲያን ወይም ማን በመባል ትጠራለች? በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ካላቸው የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በተጨማሪ ያካተተቻቸው መጻሕፍት ስንትና የትኞቹ ናቸው?

3) ካቶሊክ፣ የኦርቶዶክስና የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት የሚቀበሉአቸው የቅዱሳን መጻሐፍት ቁጥር ግለጽ።
   - ካቶሊካዊት ቤ/ክ___________________
   - ኦርቶዶክሳዊት ቤ/ክ_________________
   - የፕሮቴስታንት____________________

   ይህ የቁጥር ልዩነት ለምን የተፈጠረ ይመስልሃል?

4) ኪዳን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ከላይ በትምህርቱ ውስጥ በተብራራ መልኩ ቀርቧል፤ ሰዎች ዛሬ ቃል ኪዳን ገቡ፤ ኪዳን አቆሙ ወይም በመካከላቸው ኪዳን አጸኑ ይባላል። ለመሆኑ ሰዎች ቃል ኪዳን ተገባቡ ወይም ቃል ኪዳን መሠረቱ ወይም ቃል ኪዳን በመካከላቸው አቆሙ ሲባል ምን ያመለክታል?